# ደስተኛ አህያ ደስተኛ ባለቤት






አበበ እና ከበደ

The Donkey Sanctuary

DFID Department for International Development

አቶ አበበ ወደ ገበያ ለመሄድ እየተዘጋጀ ነው።



አቶ ከበደ ወደ ገበያ ለመሄድ እየተዘጋጀ ነው።




እንደምን አደርክ ከበደ። አንተም ዛሬ ወደ ገበያ ትሄዳለህ እንዴ?
እንደምን አደርክ አበበ። አዎ አህያው እንደተነሳልኝ እሄደለሁ።


ኦሽ አንተ ልግመኛ ፍጡር ከዚህ
በላይ መፍጠን አትችልም ማለት ነው።


አህያ በስርአት መንዳት
አትችልም እንዴ ሰውዬ፧



አቶ አበበ ከገበያው ደረሰ።
እኔ ምርቶቼን ሸጬ እስክመለስ ድረስ ከዚህ ጥላው ስር አረፍ ብለህ ቆየኝ። እዘያ ሳለህ ትንሽ መኖና_ውሃ እሠጥሀለሁ። ምናልባት ከቀናኝና በጥሩ ዋጋ ከሸጥኩ ለልጆቼ ደብተር መግዣና ለእቁብ የሚሆን ገንዘብ ይተርፈኝ ይሆናል።


ገበያው እንዴት ነበር፧?
ማለዳ ላይ ጥሩ ነበር፡፡አሁን ግን ቀንሷል
የኔ አህያ ልግመኛና አስቸጋሪ ስለሆነ ጥሩ ዋጋ አመለጠኝ፡፡ አሁን ምርቶቼን የግድ መሸጥ አለብኝ፡፡ በኋላ እንገናኝ፡፡
ከበደ ጭነቱን ከአህያው ላይ አወረደው፡፡ ነገር ግን ገበያው በውስጡ ካሉት ጥቂት ገበያተኞች በስተቀር ባዶ ነበር፡፡
ከአድካሚ የገበያ ውሎ በኋላ ከበደ አህያውን ይዞ ከገበያ ወጣ፡፡
አንተ ደደብ አህያ ፈጠን ብለህ ብትሄድ ኖሮ ምርቶቼን በደህና ዋጋ ለመሸጥ እችል ነበር፡፡ ይሄ ሁሉ ያንተ ጦስ ነው፡፡ ለምን ይሆን እንዲህ ቀርፋፋና ልግመኛ የሆንከው?፧


ደህና ዋልክ አ በበ። ገበያው እንዴት ነበር?፤
ጥሩ ነበር ማልጄ ስለደረስኩ ምርቶቼን በጥሩ ዋጋ ለመሸጥ ችያለሁ ስመለስ ደግሞ እላይ ሰፈር ለሚኖረው ተስፋዬ ሲሚንቶ ጭኜለት ስለመጣሁ ተጨማሪ ገንዘብ አግኝቻለሁ። አሁን ለልጆቹ ደብተር መግዣና ለዕድር የሚሆን በቂ ገንዘብ አለኝ።
50ኪግ


የአበበ አህያ ጭነቱ ወርዶለት ከሌሎች የቤት እንስሳት ጋር ጥላው ስር ንፁህ ውሃ ተሰጥቶት ይጠጣል።


አቶ አበበ ባለቤታቸውና ልጆቻቸው መክሰስ እየበሉ ሳለ አቶ ከበደ አዝኖ አህያውን እየነዳ ወደ ቤት ሊመለስ ተመለከቱ።


በቀጣዩ ቀን የሰፈሩ እድር ወርሀዊ ክፍያ ሊሰበስብ ተሰየመ።
እንዴት ነው ይህን ሰሞን ከእኔ ቀድመህ ገበያ ለመድረስ የምትችለውና ለእድር የምትከፍለው የማታጣው?


ለአህያዬ የተሻለ እንክብካቤ ማድረግ እንዴት እንደምችል ከተማርኩ ጀምሮ አህያዬ ጠንካራ ና ትጉህ ሆኗል። አሁን ከቀድሞው በተሻለ ሁኔታ በቀን ውስጥ የተለያዩ ስራዎችን ለመከወን ችያለሁ። ለምን ነገ ቤቴ አትመጣም፤ የተማርኩትን ሁሉ አሳይሃለሁ።


በቀጣዩ ቀን
እንደምን አደርክከበደ። መቼ ነበር ለአህያህ ለመጨረሻ ጊዜ የጥገኛ ትሎች መከላከያ መድሀኒት የሰጠከው?
እንደምን አደርክ አ በበ። አረ እኔ ምንም አይነት መድሀኒት ሰጥቸው አላውቅም። አንደኛ ነገር ውድ ነው። ደግሞም አያስፈልገውም።
እኔ ግን በአመት ሁለት ጊዜ መድሀኒቱን እሰጠዋለሁ። የጥገኛ ትሎች መከላከያ መድሀኒቱ ጥገኛ ትሎቹን ስለሚገላቸው አህያው የሚመገበውን መኖ በሙሉ ያለምንም ተቀናቃኝ ይጥቀምበታል። በመሆኑም የሰውነቱ ጡንቻዎች ስለሚዳብሩ ምንም አይነት ገጣባ ሰውነቱ ላይ የለም።
የጥገኛ ትሎች መከላከያ መድሀኒቱን ከየት አገኘ'ኸው?
ከእንስሳት ጤና አማካሪ ከግብርና ሱቅ ወይም አንዳንድ ጊዜ ከአህያ ጤናና እንክብከቤ ኘሮጀክት ተንቀሳቃሽ ክኒሊኒክ በነፃ ማግኘት ይቻላል።
እንዴት የአህያ ጤናና እንክብካቤ ኘሮጀክት ተንቀሳቃሽ ክሊኒክ በነፃ ሊሰጥ ይችላል? መድሀኒቱ እኮ በጣም ውድ ነው።


በእንግሊዝ አገር  የአህያ ጤናዋ የተሰኘ የእርዳታ ድርጅት አለ። ድርጅቱ መድሀኒቱን በነፃ ይለግሳል። ተንቀሳቃሽ ክኒሊኩ በመጣ ጊዜ የአህያዬን እግሮችም አይቷቸዋል። የአህያው እግሮች ህክምና የሚያስፈልጋቸው ከሆነም ያክሟቸዋል።
የአህያውን እግሮች ማሳየት ደግሞ ለምን አስፈለገ፤ የእኔ አህያ እግሮች ታክመው አያውቁም።


እኛ ጥፍሮቻችን ሲያድጉ መቁረጥ እንዳለብን ሁሉ አህዮችም እግራቸውን መታየት አለባቸው። ነገር ግን የአህያን እግር ማፅዳትና ማከም የሚችል ባለሙያ ብቻ ነው ይህን ማድረግ ያለበት። የአህያ ጤናና እንክብካቤ ፕሮጀክት የእንስሳት ህክምና ማዕከሉ ካስፈለገ ያንተን አህያ እግሮችም ሊያይልህ ይችላል።
ለአህያህ ትናትንት ምን ያህል ውሃ ሰጠኸው?
ጠዋት ከፍየሎቹ ጋር ጠጥቷል።


የኔ አህያ በብዛት በቀን ሁለት ጊዜ ውሃ ይሰጠዋል። ለምሳሌ ትናንት ሶስት ጊዜ ተሰጥቶት ነበር። ገበያ እንደደረስን ጭነቱን አውርጄለት እኔ ግብይቴን እስክጨርስ ድረስ ወደ ጥላው ወስጄ እንዲያርፍ፣ ሳር እንዲግጥና ውሃ እንዲጠጣ አድርጌያለሁ።
አህዩች ይህን ያህል ውሃ በተደጋጋሚ መጠጣት አያስፈልጋቸውም


በርግጥ አህዮች በጥቂት ውሃ ለረጅም ጊዜ በመቆየት ከሌሎች እንስሳት ይሻላሉ። ቢሆንም ግን የሚመገቡትን በሙሉ ስራ ላይ ለማዋልና እንዲፈጭ ለማድረግና ቆሻሻ ከሰውነታቸው በላብ መልክ እንዲወጣ ስለማረዳቸው ብዙ ውሃ ቢጠጡ ይመረጣል።


አህያዬ ጀርባው ላይ የማደርግለት ንጣፍ እጅግ ተስማምቶታል።
ለምን?


ከዚህ ቀደም አህያው ጀርባ ላይ ምንም አይነት ንጣፍ አላደርግም ነበር። የምጭነውም በቀጭን መጫኛ ነበር። የአህያ ጤናና እንክብካቤ ህክምና ማዕከል ባለሙያ እንዳስረዳኝ ከሆነ ግን የአህያው ጀርባ እንዳይቆስልና እንዳይገጣጠብ ንጣፍ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም ንጣፍን ከገለባ፣ ከአሮጌ ልብስና ከጥጥ ማዘጋጀት እንደሚቻል ባለሙያው አሳይቶኛል።


ሸክሙን በሰፋ መጫኛ አስረዋለሁ። መጫኛው የአህያውን ቆዳ በሚፈልግበት ቦታ ላይ ለምሳሌ ጭራው ስርና ደረቱ አካካቢ ተጨማሪ የጨርቅ ንጣፍ አደርግለታለሁ። አሁን አህያው ምንም ገጣባ ስለሌለበት ጠንካራ ሰራተኛና ደስተኛ እንስሳ ሆኗል።


ከዚህ በላይ ልትጭነው ትችላለህ እኮ።
ነገሩስ ይቻል ነበር። ነገር ግን ሩቅ መንገድ ስለምንጓዝ በጥሩ ጊዜ መድረስ እፈልጋለሁ።
ታስታውስ እንደሆነ ትናንትና ካንተ ያነሰ ምርት ይዤ ነበር ወደገበያ የወጣሁት። ነገር ግን አንተ ገና ከገበያ ስትደርስ እኔ ጨርሼ እየወጣሁ ነበር። ወደ ቤት ስመለስም አህያው ስላልደከመ ለተስፋዬ ሲሚንቶ ጭኜለታለሁ። አንተ ከገበያ በተመለስክለት ሰአት እኔ ከብቶች ስጠብቅ አሕያዬ ከባለቤቴና ከልጆቼ ጋር ጋር ውሀ ለማምጣት ተሰማርቶ ነበር
ባለቤቴ ትናንትናም ሁሌም እንደምታደርገው ውሃ ለመቅዳት ሄዳ ነበር።
የኔ ባለቤት በአህያው ስለምትጠቀም ውሃ ለመቅዳት የምትሄደው በሁለት ቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው።
አቶ አበበና አቶ ከበደ የአበበን አህያ ይዘው ወደ ከተማ እየሄዱ ነው።
አህያህ በጣም ትጉህ ነው። የታዘዘውን ሁሉ ይከውናል።
በሚገባ የሰለጠ አህያ እጅግ ጠቃሚ ነው። ስራህን በፍጥነት ልትከወንበት ትችላለህ ለሰፈር ሰዎችም ሳውሳቸው በቸገረኝ ጊዜ ውለታውን ይመልሱልኛል። ለምሳሌ በእርሻ ጊዜ ጥማድ በሬያቸው ያውሱኛል።



አህያዬ ልግመኛና አስቸጋሪ ከሆነ ጀምሮ ሰዎች የኔን አህያ ለመዋስ መምጣታቸውን ትተዋል። የዘንድሮን ዘር ስዘራም ማረሻ የሚያውሰኝ ሰው ስለቸገረኝ በጣም ዘግይቼ ነበር የዘራሁት።
እኔ አህያዬን በሚገባ ለሚንከባከቡ ሰዎች ብቻ ነው የማውሰው። ያዋስኩት ሰው በሚገባ ሊንከባከባው ካልቻለ ግን ዳግመኛ ለዛ ሰው አልሰጠውም።
እንደዛ ከደረክማ ሰዎች ይቀየሙህና በችግርህ ጊዜ ሊደርሱልህ አይፈቅዱም።
መቼም አህያው ታሞ ለህክምናና ለመድሀኒት ከማውጣት አልፎ ተርፎም እስኪያገግም ድረስ በሱ መጠቀምም ሆነ ማከራየት ሳልችል ብዙ ከመቸገር አይብስብኝም።
በዘያው ቀን እረፋድ ላይ በአበበ መስክ ውስጥ።
ለአህያህ ትናንት ምን ያህል መኖ ሰጠኸው?
ማታ ጫካ ውስጥ እንዲግጥ ለቅቄው ነበር።
እኔ ቅድም እረፍት እንዲ ወስድ አድርጌ ጥቂት ድርቆሽ ስጥቼዋለው። ጧት፣ ከሰአት በኋላና ሊመሻሽ ሲል ደግሞ እንዲግጥ እለቀዋለሁ። ማታ ፍየሎቹንና በጎቹን ሲጠብቅ የነሱን መኖ ተጋርቶ ይመገባል።


አህያህ ፍየሎችንና በጐቹን ይጥብቃል?
አዎ አሕያዬ በተለይ ጅቦች በረት አካባቢ ከተጠጉ ድምጽ ስለሚያሰማ ከመጣባቸው አደጋ ያመልጣሉ። ሌላው ነገር ደግሞ ከሌሎች እንስሳት ጋር ሲውል ፀጥተኛና ሰላማዊ ይሆናል።
እስቲ የኔንም አህያ ከሌሎች እንስሳት ጋር አድርጌ እሞክረዋለሁ ጩኸቱ በጣም ስለሚረብሽ ጐረቤቶቼ ቅር እየተሰኙ ነው።


አሁን ደግሞ ምን ልትሰጠው ነው ፧ እርግጠኛ ነኝ ጠዋትና ከሰአት በኋላ ግጦሽ ስለዋለ በቂ መኖ አግኝቷል።
ለአህያው ጥቂት የጤፍ ገለባ እየሰጠሁት ነው። ነገር ግን እንደተገኘው ነው። የአትክልት ምራጭም ቢሆን እስካልተበላሸ ድረስ ምንም አይልም። አህያው ብዙ ስራ መከወን ባለበት ጊዜ ለግጦሽ የሚሆን ጊዜ ስለማይኖር ተጨማሪ መኖ እሰጠዋለሁ።


እንዲሁም ጨውና ሌሎች ንጥረ ምግቦች እሰጠዋለሁ። አልፎ አልፎ ከጥራጥሬ ሽፋን ወይም ገለባ የሚዘጋጅ መኖ እሰጥዋለው።
ጨው ደግሞ ምን ያደርግለታል?


ለከብቶች ጤንነት ጨው እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ አህያዎችም ጨውና ሌሎች ንጥረ ምግቦች ያስፈልጉዋቸዋል። ነገር ግን ንጥረ ምግቦችን ዩሪያ የሌለው መሆኑን አረጋግጥ። ምክንያቱም ዩሪያ ለአህዮች መርዛማ ንጥረ ምግብ ነው።


አመሰግናለሁ አበበ ዛሬ ካንተ የተማርኳቸውን ጠቃሚ ነገሮች ሁሉ ለማስታወስ እሞክራለሁ። የኔም አህያ በቅርቡ እንደ አንዳንተው ጥሩና ፈጣን እንዲሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ነገ ከሌሎች እንስሳት ጋር እንዲሆን በረቱን አሰፋለታለሁ።
ከፈለክ ነገ መጥቼ ልረዳህ እችላለሁ።
አመሰግናለሁ። በጣም ደግ ሰው ነህ። ደህና እደር አበበ።
ደህና እደር ከበደ ።


በቀጣዩ ቀን
እንደምን አደርክ አበበ አህያው የት ነው ያለው?
እንደምን አደርክ ከበደ። አህያው ግጦሽ ላይ ነው ደግሞም ከነጋ የበቆሎና የገብስ ገለባ ሰጥቼዋለሁ።
አሁን ስራውን መጀመር እንችላለን አህያውን ይገፍው ልምጣና እንጨት በማጓጓዝ ይረዳናል።
ጥሩ አድርገሃል። አሁን በረቱን ሰፋ አድርገን መስራትና ማጠናከር አለብን። አየህ በረቱ ጠንካራከሆነ ለሌሎች እንስሳትና ለአህያውም ደህንነት አስተማማኝ ይሆናል።


አይ ተወው። አህያው ለዛሬ ይረፍ በዛውም የጀርባው ቁስል ያገግምለታል። ለዛሬ የኔን አህያ እንጠቀማለን።
እሺ እዛው ግጦሽ ሜዳ ላይ ይሁን።
ለመሆኑ አህያው መጠለያ አለው?
መስኩ ላይ ጥቂት ዛፎች አሉ። በነሱ ነው የሚጠለለው።
ዛፎቹ ከፀሀይ ከንፋስና ከፀሀይና ከዝናብ ይከላከላሉ ብለህ ነው ፤
የኔ አህያ መጠለያ ከንፋስ ከፀሀይና ከዝናብ እንዲከለከለው ዛፎች ስር ነው የተሰራው።
ለኔ አህያስ መጠለያ መስራት አንችልም?
እንዴታ ከበቆሎ አገዳ በቀላሉ መስራት ይቻላል። ነገር ግን ፋንድያውንና ሽንቱን ለማስወገድ ቦይ በመቆፈር መጠለያውን ንፁህ ማድረግና አህያውን ከበሽታ መከላከል ይኖርብናል።


መጠለያው ጥሩ ሆኖ ተሰርቷል። አህያው እንደሚስማማው ተስፋ አደርጋለሁ?
አዎን መቼም በዚህ ከቀጠልክ ጠንካራና ጤነኛ አህያ ይኖርሀል።
በስራው ስላገዝከኝ በጣም አመሰግናለሁ አበበ ። በቅርቡ መጥቼ እጠይቅሀለሁ።


ከጥቂት ሳምንታት በኋላ
አህያው ጤነኛ ሆኗል ቁስሎቹም ድነዋል። ለጀርባው ንጣፍ ታደርግለት ጀመር እንዴ?
የአህያው ጤናና እንክብካቤ ፕሮጀክት ተንቀሳቃሽ ክንሊክ ወደመንደራችን መጥቶ በነበረበት ጊዜ የጤና ባለሙያ ቁስሎችን አከመለት ንጣፍ እንዴት ማዘጋጀት እንደምንችልም አሳየኝ። አሁን የአህያውን ቆዳ የማፈገፍግ ምንም ነገር ስለሌለ ቁስሎቹ ድነውለታል።


የአህያው መጠለያ በጣም ንፁህ ነው። ጨውና ንጥረ-ምግቦች እንደገዛህና በቂ ውሃ ንደምትሰጠውም ተመልክቼያለሁ። እና አሁን ሁሉም ነገር እንዴት ነው ?
አሁን አህያዬ ቧትና ማታ እሰጠዋለሁ።በተጨማሪ ብዙ ስራዎች ሲሰራ ከዋለ ተጨማሪ መኖ ሰጠዋለሁ።


እናስ ከበደ አህያህ አሁንም ልግመኛና ቀርፋፋ ነው?
አሁን በጣም እየሠራ ነው ባለቤቴም ማገዶ ለመልቀምና ውሀ ለማምጣት ውሀለማምጣት ትጠቀምበታለች


እኔን በእርሻ ላይ እና ወደ ገበያ በግዜ ለመድረስ ይረዳኛል


ከመንደራችን ጥቂት ሰዎች ተውሰውት ነበር። እናም በአጨዳ ወቅት ሊያግዙኝ ቃል ገብተዋል።


ሌሎቹን እንስሳትን ይጠብቃል።ፀጥተኛም በመሆኑም ጐረቤቶቼ ቅሬታቸውን አንስተዋል።አሁን የተሻለ እንክብካቤ ስለማደርግለት ለቤተሰቤ የተሻለ አገልግሎት እየሰጠን ይገኛል።



አሁን የርሶን አህያ ይመልከቱ የሚያደርጉለትን እንክብካቤም ከአቶ አበበና ከአቶ ከበደ ጋር ያነፃፅሩ።

1. ለአህያው ለመጨረሻ ጊዜ የጥገኛ ትሎች መከላከያ መድሀኒት የሰጡት መቼ ነበር?
2. የሚሰጡትን ውሃ ይመልከቱ።ንፁህ ነው ? በቂ ነው ?
3. አህያው ጀርባ ላይ የሚያደርጉለትን ንጣፍ ያስተውሉ ሊሻሻል የሚችል ይመስሉታል? ከአህያ ጤናና እንክብካቤ ህክምና መአከል ወይንም በአቅራቢያዎ ከሚገኝ የእንስሳት ጤና አማካሪ ጋር ይወያዩበት።
4. መኖውን ይመልከቱ ።አህያዎ በቀን ስንት ጊዜ ለግጦሽ ይሰማራል? ተጨማሪ መኖ ይሰጡታል? በቂ ነው ይላሉ? ለአህያዎ ጨው ይሰጡታል?
5. የአህያዎ እግሮች መታየት ያስፈልጋቸዋል?

እባክዎን ጥያቄ ካሎት በአቅራቢያዎ ለሚገኝ የአህያ ጤናና እንክብካቤ ፕሮጀክት የህክምና ማዕከል ወይንም በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የእንስሳት ጤና አማካሪ አልያም ደግሞ እንደነአቶ አበበ ካሉ ጐረቤቶችዎ ያቅርቡና ይወያዩባቸው።